# ምድብ አምስት (ከ10ኛ — 12ኛ) ክፍል

## 24 ኛ ሳምንት

### *ራስን መፈለግ*

*ዓላማ*

- *መንፈሳዊ ደረጃችንን ለመፈተሽና እግዚአብሔር የሠጠንን ጸጋ እየተጠቀምንበት መሆኑን ለማወቅ፣ ከእርሱ ጋር ያለንን አንድነት ለማሳደግ ምን ማድረግ እንደሚገባን መማር መሠረታዊው የትምህርቱ ዓላማ ሲሆን፤*
- *በቃለ እግዚአብሔር በመመርኮዝ ራሳችንን መጠየቅና በእግዚአብሔር ፊትና ለኅሊናችን እውነተኛ መልስ  በመስጠት የትምህርቱን መሠረታዊ ዓላማ ማሳካትም ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል፡፡*

**የሚጠና ጥቅስ**

- ***"አንተ የማን ነህ? ወዴትስ ትሄዳለህ? በፊት ያለው ይህስ የማን ነው?"*** ዘፍ. 32÷16

*መግቢያ*

- በቤተክርስቲያን *ሥርዓት* 6ኛው የዐቢይ *ጾም* ሳምንት ገብርኄር ይባላል፤ትርጉሙም *ታማኝ* አገልጋይ ማለት ነው፡፡ "
- *ኃይለቃሉም ጌታችን መክሊታቸውን ላተረፉ ሰዎች **"አንተ በጎ ታማኝም ባርያ በጥቂት ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ"*** ማቴ. 25÷21 ብሎ በምሳሌ ካስተማረው የተወሰደ ነው፡፡
- በዚህ *መሠረትም* ይህ ሳምንት ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጠንን *መክሊት* በአግባቡ አትርፈን ለፍርድ ቀን እንድንዘጋጅ፣ጸጋችንንም በ እንድንጠቀምበት የምታስተምርበት፤እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋናአድሜ በአግባቡ ተጠቅመው ጉዞኣቸውን የፈጸሙ የሚታሠቡበትም ነው፡፡
- በዚሁ ላይ ተመርኩዘንም *መንፈሳዊ ደረጃዎቻችንና፣* ከእግዚአብሔር *ጋር ያለን* ኅብረት እንዴት ነው ? *እያተረፍን* ነው? ወይስ እየቀበርን?......ለሚሉት የምንመልስበት ነው፡፡
- *ራስን መፈለግ* በጣም ጠቃሚና ውጤታማ የሆነ *መንፈሳዊ* ጥረት ነው፡፡የጠፋው ልጅ ምሳሌን አስታውሱ ወደ አባቱ ለመመለስ *ያበቃው* የመጀመሪያ ደረጃ ***"ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ...."*** *ሉቃ* 15÷17 የሚለው ነው፡፡ይህም ራሱን አንዲያውቅና እንዲመለስ አስቻለው፡፡
- *ያዕቆብ* ከወንድሙ *ጋር* ለመገናኘት ሲጓዝ የተጠቀመበትን ጉዞ በጥልቀት ከልሱ፡፡ *ያዕቆብ* ወንድሙን በጣም ፈርቶታል፡፡እግዚአብሔርን ጠይቆና ተገልጦለትም ጥሩ  ዝግጅት አድርጎ ተጓዘ፡፡ ዘፍ. 31÷3, 32÷1-12
- የእቅዱ አንድ ክፍልም *መልእክተኞችን* ወደ ሌላው *መላክ* ነበር፡፡ ዘፍ. 32÷13-21፡፡ለኤሳው ስጦታ አስይዞ አዘጋጃቸው፡፡***"አንተ የማን ነህ? ወዴት ትሄዳለህ?በፊትህ ያለው ይህስ የማን ነው?"***የሚሉ *ሦስት* ቁልፍ *ጥያቄዎችንም* ከትክክለኛ *መልሶቻቸው ጋር* አዘጋጀ፡፡በዘፍ. 32፤33 እንደተገለጠውም የሁለቱ ወንድማማቾች ግንኙነት የተሳከ ሆነ፡፡
- እነዚህን *ሦስት መሠረታዊ ጥያቄዎች* በትክክል ጠይቀን በእውነትና፤በድርጊት ከመለስናቸው ከአምላካችንና ከጌታቸን *ጋር* ያለንን ግንኙነትና *መንፈሳዊ* ሕይወታችንን እናሻሽላለን፡፡በጌታ ፊት የምንመልሰው፣የምናቀርበው በጎ ነገር፣ትርፍም ይኖረናል፡፡እንደ ገብርኄር- ***'ወደ ጌታህ ደስታ ግባም'*** እንባላለን፡፡

**የትምህርቱ ዋና ይዘት**

**እያንዳንዳችን የተሰጠን 'መክሊት' አለ፡፡**

- ሰጪውም እግዚአብሔር ሲሆን የተሰጠበት ዓላማም አትርፈን እንድንመልስ ነው፡፡ ***"የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው፤መንፈስ ግን አንድ ነው፤አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤ አሠራም ልዩ ልዩ ነው÷ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው፡፡ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል፡፡ ..... ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያከፈለ ያደርጋል፡፡... እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል፡፡ ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል፡፡"*** 1ኛ ቆሮ. 12÷4-13 እንዲል፡፡መንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ጠቅመን ሌላውን የምንጠቅምበት የጸጋ ስጦታዎች ለእያንዳንዳችን አድሎናል፡፡
- በተጨማሪም እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው ***"እንደተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን ትንቢት ቢሆን አንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማር ይትጋ፤ የሚመክርም ቢሆን በመምከር ይትጋ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ የሚገዛ በትጋት ይግዛ ሚምር በደስታ ይማር፡፡"***ሮሜ. 12÷6-8
- አባቶቻችንና እናቶቻችን ይሄን አውቀው ታምነው ተሠማሩ÷ ሩጫቸውንም ፈጽመው የጽድቅን አክሊል ተቀበሉ፡፡ ***"መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ÷ሩጫውን ጨርሼአለሁ÷ ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ፤ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል÷ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል÷ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም፡፡"*** 2ኛ ጢሞ. 4÷7-8
- ይህን ተስፋም ጌታችን ለባለ ራዕዩ (አቡቀለምሲስ) ዮሐንስ እንዲህ ሲል ገልጾለታል፡፡

*"ባርያዎቹም ያመልኩታል ፊቱንም ያያሉ÷ስሙም በግምባሮቻቸው ይሆናል። ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም÷ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና ፀሐይ አያስፈልጋቸውም፤ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ።እርሱም እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኛዎች ናቸው።....የሚጠብቅ ብፁዕ ነው አለኝ።"ራዕ.* 22÷3-7

- ሰማዕታት ለሕይወታቸው ያልሳሡት ፣ ጻድቃን ዓለምን ጥለው የመነኑት፣ ሊቃውንት አበው ሙሉ ሕይወታቸውን ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲመረምሩና ሲያስተምሩ የኖሩት ይሄን ተስፋ ለማግኘት ነው።
- እኛም በተሠጠን ጸጋ እንሠማራ። ***"ጻድቅ ጌታ" - "አንተ ታማኝ በጎም... ወደ ጌታህ ደስታ ግባ*** ...የሚለውን ቃል ለመስማት ተስፋውንም ለማግኘት ጉድለታችንን አርመን በጸጋችን ለመስማራት ከላይ በተጠቀሰው ታሪክ ተመርኩዘን ራሳችንን እንጠይቅ....

**የመጀመሪያው ጥያቄ፡ <u>አንተ የማን ነህ?</u>**

- የዚህ ጥያቄ ሐሳብ በነፍስህ፣ በልብህና በፍላጎቶችህ ሥልጣን ያለው ማነው? ሕይወትህንና ጠባይህን እንዲመራው የፈቀድክለትስ ለማን ነው? የሚል ነው።

<u>ገንዘብ በእናንተ ላይ ሥልጣን አለው?</u>

- በመጽሐፍ ቅዱስ ገንዘብ የሚያመልኩና ገንዘብ ሙሉ ሥልጣን በላያቸው ስለነበረው ሰዎች በብዙ በምሳሌ ተጽፎል።
- የአስቆሮቱ ይሁዳ ጌታውን የሸጠው ለገንዘብ ነበር።በኋላም ተጸጽቶ ራሱን አጥፍቶል።
- የዘላለም ሕይወት እንዳገኝ ምን ላድርግ። ብሎ የጠየቀው ባለጠጋም ጌታችን ለድሆች እንዲመጸውት ሲነግረው ገንዘቡን መርጦ ***"እያዘነ ተመለሠ" ማር.*** 10÷17-22
- ስለዚህ ገንዘብ፡-ከእግዚአብሔር መንግሥት የሚያወጣን ሌላ ጌታ ሳይሆን ጽድቅ የምንሠራበት፣ ለፍላጎቶቻችን መሟላት የምንጠቀምበት መሣሪያ ነውና። ልንጠቀምበት እንጂ ሊያዘን አይገባም።

<u>**ውጤት**</u> ገንዘብ ኃይለኛ ጌታ ነው።በድካም ይሰበሰባል፣ በፍርሃት ይጠበቃል፣ በሀዘን ትቶም ይሄደል።

<u>ኃጢአት በእናንተ ላይ ስልጣን አለው?</u>

- ***"ለኃጢአት የተገዛ የኃጢኣት ባርያ ነው።"*** ይህም ማለት "ዲያብሎስ በኃጢአተኛ ነፍስ ላይ ሥልጣን አለው ማለት ነው።ያ ሰውም የኃጢአትና ዲያብሎስ ባርያ ነው።"

<u>**ምሣሌዎች**</u>፡የሶምሶንን ታሪክ ተመልከቱ።/መሳፍንት 16/ ሶምሶን የእግዚአብሔር መንፈስ በርሱ ላይ ነበርና እጅግ ጠንካራ ነበር። አንድ ወቅትም 1000 ሺህ ፍልስጤማውያንን ድል አድርጎል። ከገሊላ ጋር በኃጢአት ሲወድቅና ምሥጢሩን ሲያወጣ ግን ደካማ ሆነ፤ፀጉሩን ቆረጠችው ዐይኑን አሳወሩትና በእስር አስቀመጡት።

<u>**ውጤት**</u>፡ ኃጢአትና ዲያብሎስ ጨካኝ ጌቶች ናቸው በባርነት ይዘው ከእግዚአብሔር ይለያሉ።

<u>**እኔ የፈጣሪዬና የመድኃኒቴ ነኝ**</u>

- እግዚአብሔር ፈጣሪዬ ነውና ለርሱ ብቻ እገዛለሁ።
- እግዚአብሔር እስከ መስቀል ወዶኛል፤ በሙሉ ልቤ የምወደውና የማመልከው እርሱን ብቻ ነው። በዚህም የሕይወቴ ንጉሥዋ የነገሥታት ንጉሥ እግዚአብሔር ነው።

<u>**ውጤቱ**</u>፡ የሰላም ሕይወት እኖራለሁ ምክንያቱም የሠላም ንጉሥ እግዚአብሔር ንጉሥዋ ነውና። በሰማይም ከእግዚአብሔር ጋር ሥፍራ አለኝ ምክንያቱም በቃል ኪዳኑ አምናለሁና።

<u>**ሁለተኛው ጥያቄ ወዴት ትሄዳለህ?**</u>

- ሁላችንም ከምድር የምንሄድበት ቀን አለና ይህን ጥያቄ መመለስ እጅግ አስፈላጊ ነው።ይሄን ጥያቄ ሲጠየቁ ብዙ ሰዎች የሚከተሉትን መልሶች ይሠጣሉ፡-

**የት እንደምሄድ አላውቅም** - አደገኛ መልስ ነው።

- መኪና የሚነዳ የሚደርስበትን ካላወቀ፤አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ነው።

**እግዚአብሔር ያውቃል እኔ አላውቅም።**

- ይሄም ጥሩ መልስ አይደለም። በርግጥ እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው ነገር ግን፤ሁለት መንገዶች እንዳሉም ነግሮናል።ቀላሉና ወደሲኦል የሚደርሰውና ወደ ገነት የሚያደርሰው ከባዱ መንገድ ናቸው። ማቴ. 7÷13-14።እግዚአብሔር እንደፈቃደ እግዚአብሔር ሁላችንም እንድንድን ይፈልጋል። ***"ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ"*** ብሏልና።

***እንደ ሥራዬ እሄዳለሁ።***

- የእኛ ሥራ ብቻውን እንደማያድነንም ቅዱስ ጳውሎስ ***"ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለምና"*** ኤፌ. 2፤9

***ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደምገባ ተስፋ አደርጋለሁ።***

- ተስፋ ብቻውን ግን በቂ አይደለም።

**የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ሲኦል አይተውኝም።**

- በዚህ ምድር ምህረት የለመኑ ይቅርታ እንዳገኙ ተጽፎል። ከሞት በኂላ ምሕረት የለመነው ካለ በጣም ዘግይቶ ነበርና ይቅርታ አላገኝም። ሉቃ 16÷19-31 ከኃጢአት ጋር መሞት፤የዘለዓለም ሞት ነውና። ራዕ. 20÷14

**ገነት እንደምገባ እርግጠኛ ነኝ።ይሄንን በተስፋ እየጠበቅኩ የታዘዝኩትንም እፈጽማለሁ።**

- አይገባኝም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው ቃልግን እኖራለሁ።የጌታዬ ደም ከኃጢአቴ ያነጻኛልና እቀርባለሁ።
- አይገባኝም ግን በእግዚአብሔር ፍቅር አምናለሁ።ባይገባኝም እስከ መጨራሻይቱ ሕቅታ ሕይወቴን ሙሉ እታገላለሁ።
- አይገባኝም ነገር ግን ሰማያዊ ሕይወትና ተስፋ ለማግኘት በምድራዊ ሕይወቴ እጥራለሁ።በጸሎት፣በሰማያዊ ፍቅርና ቅዱሳንንም በመማጸን እኖራለሁ።

***ሦስተኛው ጥያቄ ይህስ የማን ነው?***

- ያለን በሙሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ነው።ጥያቄው እንዴት እንጠቀምበታለን ነው? አንዳንድ የእግዚአብሔር ስጦታዎችን አንስተን እንይ፦

***ጤና*** ***"ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?"***1ኛ ቆሮ. 6÷19 ጤናውየተጠበቀለትን ሥጋዊ አካላችንንና አቅማችንን ለመንፈሳዊ እድገታችን (ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ ትጋት...)ለቤተክርስቲያን እድገት በመድከምእናለኀብረተሰባችንእድገትና ለውጥ ጠቃሚ ነገሮችን ለመፈጸም እናውለው።

***"የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፤ ደስ አያሰኙም የምትላቸውም ዓመታት ሳይረደርሱ፤"*** መክ. 12÷1 ተብሎ እንደተጻፈ።ጤናችንንና የወጣትነት ኃይላችንን በአደንዛዥ እጾች፣በስካር፣በዝሙትም አናባክነው የባለቤቱ መጠቀሚያ ቤተመቅደስ ይሁን እንጂ።

***ገንዘብ***፡ አስራት በማውጣት፣በአግባቡ ለሚያስፈልገን የምንጠቀምበት ነው።ይሄን ስናደርግም ***"በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራቱን ሁሉ ወደጎተራአግቡ ...በረከቴንም አትረፍርፌ ባለፈስባችሁ በዚህ ፈትኑኝ ይላል÷ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።"*** ሚልክ. 3÷10

***ጊዜ*** መጽሐፍ ስለ ጊዜ ***"ለሁሉ ዘመን አለው÷ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው።"*** መክ. 3÷1 እኛስ ጊዜያችንን እናባክናለን?ወይስ በአግባቡ እንጠቀማለን ?ጊዜ አጠቃቀም በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።በአንድ ከተማ የቆመ ሰዓት ሥር ***"በፍጹም ወደ ኋላ አይሄድም"*** ተብሎ ተጽፎል።የተሰጠንንመክሊት ልናተርፍበት የተሰጠን ነውና፤ጊዜያችንን ውጤታማ ማድረግ አለብን።

***ማጠቃለያ***

1. ራሳችንን በግልጽ እንወቅ። የእግዚአብሔር ልጆች ከሆን በጥንካሬ እንክተለው።የልባችን መሪም እናድርገው።በየትኛውም የሕይወታችን አቅጣጫም በመሪነት እንዲቀድመን እንጥራው።
2. የእግዚአብሔር መሪነት ጥቅማችን፤አስፈላጊያችንም መሆኑን ካመን።ሌሎቹን ከልባችን እናውጣ።***"መንገዱን ጥረጉ ጥርጊያውንም አቅኑ።"***ተብሎልና። ማቴ. 3÷3
3. ለዘላለማዊ ሕይወታችን እንሥራ።ሰማያዊ ሕይወታችንን የሚያቃናልን ሥራ በየእለቱ እናከናውን። ዛሬስ ለዘላለማዊ ሕይወታችን ምን ሠራን ?
4. ያለንን ሁሉ የሠጠን እግዚአብሔር ነው።በመጨረሻው ቀንም ሊቆጠርንና ምን ሠራችሁበት ሊለን ይመጣል።የተሠጠንን እንደ **ገብርኄር** በጥንቃቄ ተጠቀመንበታል? ወይስ ቀብረነዋል? በአፋጣኝ መልስ ዛሬ እናንሳ።ነገ የኛ አይደለም። ***"ለነገ አትጨነቁ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል።"*** ማቴ 6÷34
5. ***"ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም የበራ ይሁን እናንተም ጌታቸው መጥቶ ደጁን ሲያንኳኳ ወዲያው እንዲከፍቱለት ከሰርግ እስኪመለስ ድረስ የሚጠብቁ ሰዎችን ምሰሉ ጌታቸው በመጣ ጊዜ ሲተጉ የሚያገኛቸው እነዚያ ባሪያዎች ብፁዓን ናቸው እውነት እላችኋለሁ÷ ታጥቆ በማዕድ ያስቀምጣቸዋል ቀርቦም ያገለግላቸዋል።"*** ሉቃ. 12÷35-37 እንደተባልን ሁሌም የተዘጋጀን፣ በመክሊታችን የምናተርፍ ጌታችንን በፍቅርና በመታመን የምንጠብቅም መሆን አለብን።

***መዝሙር***

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ይጠብቀኛል
በእረፍት ውሀ በለምለም መስክ እኔን ይመራኛል።

***ይቆየን።***